በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች
ክልል መንግሥት
የትምህርት ቢሮ
Southern Nations, Nationalities and Peoples
Regional Government
Education Bureau

ቁጥር 66/ከ49-1856/ከ10 49
Ref. No
ቀን 02/12/2000
Date

ለ ሀዲያ ዞን ትምህርት መምሪያ
ሆሳዕና ፤

ለ________ ልዩ ወረዳ ት/ጽ/ቤት
________፤

ለሃዋሳ ከተማ አስተዳደር ትም/አቅ/ግን/መምሪያ
________፤

ጉዳዩ፦ የርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሥራና የደረጃ ዕድገት መመሪያ ስለመላክ

ከቢሮአችን ተዘጋጅቶ ከሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ እንዲውል ለሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ የተላከው የርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሥራና የደረጃ ዕድገት አፈፃፀም መመሪያ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ፀድቆ በቀን 28/11/2000 በቁጥር ደኢ/ርመ101/9329 የተላለፈላቸውን የክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ በሥራ ላይ እንዲውል በማለት በቀን 30/11/2000 ዓ.ም በቁጥር ደኢ/ጠ03/21/230/2228 በተጻፈ ደብዳቤ ገልጾልናል፡፡

ስለዚህ መመሪያው ኮፒ ተደርጎ ለወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲደርሳቸውና በመመሪያው መሠረት ተግባራዊ እንዲደረግ 24 ገጽ ኮፒ መላካችንን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

ማቴዎስ ማልዳዮ
የመምህራን፣ የርዕሰ መምህራንና
የሱፐርቫይዘሮች አስተዳደር
የሥራ ሂደት ባለቤት

ግልባጭ፡
- ለትም/ቢሮ ኃላፊ ጽ/ቤት
- ለምክትል ቢሮ ኃላፊ ጽ/ቤት (2)
- ለትም/ሥልጠና ጥራት ማረጋገጫ ዋና የሥራ ሂደት
- ለመም/ቴክ/ባለሙያዎች ልማት የሥራ ሂደት
- ለመርሱ አስት/የሥራ ሂደት
- ለሕዝብ ግንኙነት
- ለክልል መምህራን ማህበር ጽ/ቤት

ት/ቢሮ

676/21/49
02/12/2000
13/12/2000

ሐዋሳ

ትምህርት ቤቶች ሥርዐተ-ፆታን ያማከለ ሊሆኑ ይገባል!!

(1) ለትምህርት ...
(2) ለአስ/ሽግ፡
23/12/20..

በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት
ለትምህርት ቢሮ
ሀ ዋ ሳ፣

ጉዳዩ:- መመሪያ ስለመላክ ፣

የርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሥራና የደረጃ ዕድገት አፈፃፀም ረቂቅ መመሪያ በማዘጋጀት ከሐምሌ 1 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ ለማዋል በሚያስችል መልኩ እንዲፀድቅ በቁጥር 45/ለ48-2479/ለ/49 በ22/09/2000 በተፃፈ ደብዳቤ መጠየቃችሁ ይታወሳል::

በዚህም መሠረት የተሟላ መመሪያ እንዲሆን ከቢሮዎ ከሚመለከታቸው ክፍሎች እንደገና በማጥናት ያቀረባችሁት መመሪያ በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ፀድቆ በቁጥር ደኢ/ርመ101/9329 በ28/11/2000 የተገለፀልን ስለሆነ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲደረግ እያሳሰብን ይህንን መመሪያ 45 ገጽ በዚህ ደብዳቤ መላካችንን በተጨማሪ እናሳስባለን ::

« ከሠላምታ ጋር »

ተሾመ ዲቢሎ ዲዳና
TESHOME DIBILO DIDENA
ዳይሬክተር
Director

በደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ
S/N/N/P/R/G/Civil Service Agency

ግልባጭ፣
በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት
- ለርዕሰ መስተዳደር
ሀ ዋ ሳ

የበ

የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት
መዝገብ ቤት
ገ/ቁ
የደረሰበት ቀን 21/12/2006
የተመራበት ቀን
ክፍሉ ...
የፋይል ቁጥር ከ49 - 1833
ለክፍሉ የተላለፈበት ቀን
የተመለሰበት ቀን

1-12-2000

የርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሥራና የደረጃ ዕድገት መመሪያ

ት/ሴ/መ/ቁ 1/2000

ደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መ/ሲ/ሰ/ኤጀንሲ
ሰኔ 2000 ዓ/ም

S/N/N/P/R/G/Civil Service Agency

II. መግቢያ

የትምህርት ስርዓታችን የሚፈለገውን የትምህርት ጥራት ለማምጣት በየደረጃው ያሉ የትምህርት አመራር አካላት በተለይም ደግሞ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ወሳኝ ሚና አላቸው።
የትምህርት ቤት አመራር ሙያ ከባድ ሃላፊነትን የሚጠይቅ ከመሆኑም ባሻገር በአሠራር ልምድ እንደታየው ውስብስብ ተግባራት የሚስተናገዱበትና መፍትሄ የሚያገኙበት በመሆኑ ሙያው የራስ ተነሳሽነትን፣ ቁርጠኝነትና የተለየ ጥረትን የሚፈልግ ነው።

ትምህርት ቤቶች ብቁ ዜጎች የማፍራት ተልዕኮአቸውን አስቸጋሪ ከአደረገባቸው አንዱና ዋናው ምክንያት ጠንካራ የትምህርት ቤቶች አመራርና አስተዳደር ያለመኖሩ ነው። በዘርፉ ስር ሰዶ የቆየውን የተዛባ አሠራርና አሉታዊ አስተዳደራዊ ተፅዕኖ በማስወገድ የሙያን ክቡርነት ጐልቶ እንዲታይ ማስቻል ተገቢ ነው። የሙያተኞችን ቁርጠኝነት ለማረጋገጥ በዘርፉ ትልቅ እመርታ ማስመዝገብ ቅድሚያ የማሰጠው ተግባር ሆኖ ተገኝቷል። ለዚህ ደግሞ በቂ እውቀትና ክህሎት ያላቸውና የሰለጠኑ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን ማፍራት ወሳኝ ነው።

ይህን ነባራዊ ሀቅ ከግምት ውስጥ በማስገባት በሙያቸው ጠንካራ የሆኑና በቂ ልምድ ያካበቱ መምህራንን በርዕሰ መምህርነትና ሱፐርቫይዘርነት በመመደብ የትምህርት ቤቶች አመራርና አስተዳደር፣ የትምህርት ድጋፍ ፣ ክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት ባለውና በተጠናከረ ሁኔታ እንዲከናወን ለማስቻል ወደ እዚህ ሃላፊነት / ሥራ የሚስብ የምደባ ሥርዓት መኖር እንዳለበት ስለታመነበት አዲስ የርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች የሥራና የደረጃ ዕድገት መመሪያ በ1995 ዓ.ም በትምህርት ሚኒስቴር ተዘጋጅቶና ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ ተዘጋጅቶ በክልሉ ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ ፀድቆ በ1996 በሥራ ላይ እንዲውል መደረጉ ይታወቃል።

መመሪያው ሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ በአተገባበር ላይ ያጋጠመ ብዙ ችግሮች መኖራቸው በተለያዩ ክልሎች ጥያቄ ቀርቦ የክልል ትምህርት ቢሮዎች በተለያዩ የምክክር ስብሰባዎችና ኮንፍረንሶች ላይ ያለው መመሪያ እንዲሻሻል ሀሳብ ሲያቀርቡ ቆይተዋል።
በመሆኑም በፌዴራል ደረጃ በ1995 ተዘጋጅቶና ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥሞ በ1996 ሥራ ላይ የዋለውን የር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የደረጃ ዕድገት መመሪያ አሻሽሎ

በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ

ዓላማ

አጠቃላይ ዓላማ

የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማስጠበቂያ ፓኬጅን በአግባቡ የማስፈፀም አቅም ያለው አስተማማኝ የተረጋጋ የአመራር ስርዓት ለመፍጠር ነው።

ዝርዝር ዓላማ

- የትምህርት ሥርዓቱን በሠለጠነና የተሻለ የሙያ ብቃት ባለው የሰው ኃይል ለመምራት፣
- አስተማማኝ የትምህርት አመራርና አስተዳደር ዕውቀትና ክህሎት ያላቸውን ባለሙያዎች ወደ ትምህርት አመራር ሥርዓቱ በማምጣት በሥራው ላይ እንዲቆዩ ለማድረግ፣
- የትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፓኬጅን በጥልቀት ተገንዝቦ በዝርዝር የማስፈፀም አቅም ያለው አመራር ለመፍጠር፣
- በዘርፉ የተሰማሩ የትምህርት ባለሙያዎች የሙያ ብቃታቸውን ማሳደግ የሚያስችል የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለመስጠትና እንደየሥራ አፈፃፀም ብቃታቸው ተመጣጣኝ የደረጃ ዕድገት ሥርዓት ለመዘርጋት፣
- ፈጣን የሰው ኃይል ቅይይርን ሥራ ለቆ መሂድን በማስወገድ ከፍተኛ ልምድና አቅም ያላቸውን ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሰጡትን አገልግሎት ግምት ውስጥ በማስገባት በአመራር ላይ እንዲቆዩ ለማድረግ፣

አስፈላጊነት

በትምህርት ስርዓታችን ለርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ተገቢ የሆነ የማትጊያ፣ የአቅም ግንባታ እና የሚስብ የደመወዝ ክፍያ ሥርዓት ስላልነበረ ጠንካራ ባለሙያዎችን በሚፈለገው መጠን ወደሙያው ለማስገባት ካለመቻሉም በላይ ወደ ሙያው የገቡትም ቢሆኑ ብዙ ሳይቆዩ ሙያውን ለቀው እንደሚሄዱ የሚታወስ ነው። በዚህም ምክንያት ት/ቤቶች በስትራቴጅክ ዕቅድ በመመራት የተጣለባቸውን ሀገራዊ ኃላፊነት መወጣት ሲሳናቸው ቆይቷል። ይህን ስር ሰዶ የቆየ ችግር ለመፍታት በ1996 ዓ.ም የርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሥራ ዕድገትና የደመወዝ ምደባ የሥራ መመሪያ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ ውሏል። ይሁን እንጂ ይህ መመሪያ ከላይ የተጠቀሱትን ወስብስብ ችግሮች በዘላቂነት ሊፈታ በሚችል መልኩ የተዘጋጀ

ምዕራፍ አንድ

የሀላፊዎች አመዳደብ ስትራቴጂዎች

በርዕሰ መምህርነት እና በሱፐርቫይዘርነት መደቦች ተወዳድረው መመደብና ውጤታማ የሆነ ስራ በማከናወን ለትምህርቱ ጥራት ጉልህ ሚና እንዲጫወቱ ማድረግ ወሳኝ ነው።

በመሆኑም ምደባና ከምደባ ጋር የተያያዙ ከንውኖች ቀጥሎ ያሉትን ስትራቴጂዎችን የተከተለ ማድረግ ተገቢ ነው። በዚህም መሠረት በቅድሚያ ለትምህርቱ ሥራ፣ በመቀጠልም የባለሙያቹን ቁርጠኝነት ለማረጋገጥ እንዲሁም በስራው ላይ አዎንታዊ አመለካከትና የስራ ውድድር ለመፍጠር የሚከተሉት ተግባራት በቅደም ተከተል ይከናወናሉ።

1.1. ምልመላ

የትምህርቱ ስራ ውጤታማነት ስራውን ለመምራት በተመደበው ሀላፊ ቁርጠኝነት ይወሰናል። ይህም የአመራሩ ሚና ወሳኝነት እንዳለው ያሳያል።ትምህርቱ የአገሪቱ ልማት ስትራቴጂክ መሳሪያ እንደመሆኑ መጠን ምንጊዜም ቢሆን አስተማማኝና ቁርጠኛ አመራር ሊኖረው ይገባል። በዚህም መሰረት የአመራሩ ምልመላ በዘፈቀደ የሚካሄድ ሳይሆን ጥንቃቄ በተሞላበት ሁኔታ የሚካሄድ ይሆናል። ስለዚህ ምልመላው ሁለት ደረጃዎች ይኖሩታል።

1.1.1. ቅድመ ምልመላ

በቀጥታ ወደ ምልመላ ስራ ከመገባቱ በፊት ወደ ውድድር የሚመጡ ባለሙያዎች ሁሉ በቅድመ ምልመላ ሂደት ውስጥ የማለፍ ግዴታ ይኖርባቸዋል።

በመሆኑም ለርዕሰ መምህርነትና ለሱፐርቫይዘርነት የሥራ መደቦች ለውድድር መቅረብ የሚቻለው በየደረጃው የሚደረገውን ቅድመ ምልመላ ሲታለፍ ብቻ ነው። ስለዚህ የሚከተሉት ነጥቦች በቅድመ ምልመላ መስፈርትነት የሚያገለግሉ በመሆኑ ተወዳዳሪዎች በቅድሚያ መስፈርቶችን አሟልተው መገኘት ይኖርባቸዋል።

ሀ) የሀገሪቱንና የክልሉን ሕገመንግሥት፣ የኢትዮጵያ የትምህርትና የልማት ፖሊሲዎችን

• ምዝገባው የሚጀመርበትና የሚጠናቀቅበት ቀንና ሰዓት፣

• የምዘገባ ቦታና የቢሮ ቁጥር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ፈተና የሚሰጥበት ቀን ያካተተ ሆኖ፣

የደረጃ ዕድገት ማስታወቂያው ቢያንስ ለ5 ተከታታይ የሥራ ቀናት በግልፅ የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ይለጠፋል። ምዝገባው ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉ 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት እንዲካሄድ ይደረጋል።

1.1.2.2. የመወዳደሪያ ርዕሶችና የመመዘኛ ነጥቦች፦

የቅድመ ምልመላ ሂደት ከተከናወነ በኋላ ለርዕሰ መምህርነትና ሱፐርቫይዘርነት ውድድር በእጩነት የሚቀርቡ ተወዳዳሪዎች በሥራ አፈጻጸም ውጤታቸው፣ በጽሁፍ ፈተና፣ በቃለ መጠይቅ ፣ በሥራ ልምድና በማህደር ጥራት ተወዳድረው እንዲመረጡ ይደረጋል። አፈፃፀሙም በሚከተለው ሁኔታ ይከናወናል።

ሀ. የሥራ አፈጻጸም ውጤት (50%)

ለውጤት ተኮር የዕቅድ አፈጻጸም የሚሰጠው ዋጋ 50% ሆኖ ለደረጃ ዕድገት ውድድር መቅረብ የሚቻለው በአራት ተከታታይ የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ከፍተኛ እና ከዚያ በላይ የሆነ ውጤት ማስመዝገብ ሲቻል ብቻ ነው። ነገር ግን በቂ በሆነ ምክንያት ተከታታይ አራት የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ውጤት በማይገኝበት ጊዜ የሁለት ጊዜ ግምገማ ሊያዝ ይችላል።

ለ. የጽሑፍና የቃል ፈተና (35%)

ዕውቀትንና ክህሎትን ለመመዘን የሚያስችል የጽሑፍና የቃል ፈተና ተዘጋጅቶ 35% ዋጋ እንዲኖረው ይደረጋል። በዚሁ መሠረት፦

- የጽሑፍ ፈተና 25%
- የቃል ፈተና 10% የሚይዝ ይሆናል። ለቃል ፈተና ለመቅረብ ተወዳዳሪው በቅድሚያ የጽሁፍ ፈተና ተፈትኖ በውጤቱ ግማሽና ከዚያ በላይ ማግኘት አለበት።

ሐ. የሥራ ልምድና የሙያ ማሻሻያ (10%)

የሙያ ማሻሻያ ትምህርት ከመደበኛ የትምህርት ደረጃ ተነጥሎ እራሱን በቻለ ሁኔታ እየተገመገመና ከክፍት የሥራ መደቡ ወይም ከሙያው ጋር አግባብ ያለው

ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግሥት ... ... SNNPRS ... Agency

ለማኅደር ጥራት የሚሰጠው ነጥብ

ተ.ቁ	የተወሰደ የዲሲፒሊን እርምጃ	የሚቀነስ ነጥብ	የሚሰጥ ነጥብ
1	የሚቀጥለውን የደመወዝ ጭማሪ የማገድ ወይም ከደረጃና ከደመወዝ ዝቅ የማድረግ ቅጣት፣	5	0
2	ከአንድ ወር በላይ እስከ ሁለት ወር ደመወዝ ቅጣት	4	1
3	የአንድ ወር ደመወዝ ቅጣት	3	2
4	የተደጋገመ ማስጠንቀቂያ ቅጣት	2	3
5	የመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ ቅጣት	1	4
6	ምንም የቅጣት ሪከርድ የሌለበት	0	5

የዲሲፒሊን ቅጣት ሪከርድ ስለሚጠቀስበት ጊዜ

- ቀላል የዲሲፒሊን ቅጣት የደረጃ ዕድገት የማይከለክል ሲሆን ቅጣቱ ከተወሰነበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ዓመት በሪከርድነት ይጠቀሳል።
- ከባድ የዲሲፒሊን ቅጣት የደረጃ ዕድገት የሚከለክል ሲሆን ቅጣቱ ከተወሰነበት ጊዜ ጀምሮ ለአምስት ዓመት በሪከርድነት ይጠቀሳል።

1.2. ምደባ

ምደባ ከምልመላ ቀጥሎ የሚከናወን ተግባር ነው። የርእስ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች ምደባ በመምህራን ልማት መርሀ ግብር ገዥ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት የሚከናወን ይሆናል። በመሆኑም፦

1. ለመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት ቤት የተማሪ ቁጥር እስከ 500 ሲሆን አንድ ርእስ መምህር፣
2. የመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት ቤት ሆኖ የተማሪዎች ቁጥር ከ500-1000 ከሆነ በተጨማሪ አንድ ምክትል ርእሰ መምህር እንዲኖረው ይደረጋል።
3. የመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት ቤት ሆኖ የተማሪዎች ቁጥር ከ1000 ያለፈ ከሆነ አንድ ርእሰ መምህርና ሁለት ምክትል ርዕስ መምህራን ይመደቡለታል።
4. ሙሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (1-8) ሆኖ የተማሪዎች ቁጥር ከ500-1000 ሲሆን አንድ ርእሰ መምህርና አንድ ምክትል ርዕሰ መምህር እንዲኖሩት ይደረጋል።
5. ሙሉ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት (1-8) ሆኖ የተማሪዎች ቁጥር ከ1000 በላይ ከሆነ አንድ ርእስ መምህርና ሁለት ምክትል ርዕሰ መምህራን ይኖሩታል።

- አንድ ምክትል ርእሰ መምህር ብቻ በሚመደብበት ትምህርት ቤት ምክትል ርእሰ መምህሩ የአካዳሚክና የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራሞችን የሚመራ ሲሆን በተጨማሪም ርእሰ መምህሩ በማይኖርበት ወቅት በርእሰ መምህሩ የሚከናወኑ ተግባራትን በሙሉ ደርቦ ያከናውናል።
- ሁለት ምክትል ርእሰ መምህራን በሚመደቡበት ትምህርት ቤት አንዱ ምክትል ርእሰ መምህር አካዳሚክ ነክ ጉዳዮችን በሃላፊነት እንዲመራ የሚደረግ ሲሆን ሁለተኛው ምክትል ርእሰ መምህር ደግሞ አስተዳደራዊና የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራሞችን በሃላፊነት እንዲመራ ይደረጋል።
- ሶስት ምክትል ርእሰ መምህራን በሚመደቡበት ትምህርት ቤት ሁለቱ የአካዳሚክ ጉዳዮችን እንዲመሩ የሚደረግ ሲሆን እንደትምህርት ቤቱ ስፋትና ደረጃ የትምህርት ክፍሎችን (ዲፖርትመንቶችን) ተከፋፍለው እንዲመሩ ይደረጋል። ሶስተኛው ምክትል ርእሰ መምህሩ ደግሞ አስተዳዳራዊና የተጓዳኝ ትምህርት ፕሮግራሞችን በሃላፊነት እንዲመራ ይደረጋል።

1.3. አቅም ግንባታ

በማንኛውም ደረጃ የሚመደቡ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በየጊዜው ካለው ፍላጎትና ከሙያው ከሚጠበቀው ወቅታዊ አሰራር አኳያ እየታዩ በፍላጎት ዳሰሳ ላይ የተመሠረተ የአቅም ግንባታ ስልጠና ይሰጣቸዋል። ለእነዚህ የትምህርት ባለሙያዎች የሚሰጠው ስልጠና የትምህርቱን ጥራት ለማጎልበት በሚያበቃ መልኩ ታስቦ የሚከናወን ይሆናል። በመሆኑም የአቅም ግንባታ ሥልጠናው በዋናነት በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ያተኩራል፣

- ዘመናዊ የትምህርት አመራርና አስተዳደር
- የሀገሪቱ ሕገ-መንግሥት፣ የትም/ፖሊሲ የትግበራ ስትራቴጂዎች አመራር
- የስትራቴጂክ እቅድ አነዳደፍና አተገባበር፣
- የሀብት አጠቃቀም
- የትምህርትን ስርአት በዝርዝር መረዳትና መተግበር
- የክትትልና ግምገማ አፈጻጸምና ስልቶች፣
- ህብረተሰቡ በትምህርቱ ሥራ ሙሉ ተሳታፊ እንዲሆን ስለሚደረግ እንቅስቃሴ፣
- ተከታታይ የመምህራን የሙያ ማሻሻያ መርኃ-ግብር
- ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን
- የስራ ላይ ማትጊያ ስርአቶችና አተገባበራቸው፣

በደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ
S/N/N/P/R/G/Civil Service Agency

1.6. የርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች አመዳደብ፣

- በዲፕሎማ የተመረቁና መስፈርቱን የሚያሟሉ ከመለስተኛ የመምህርነት ደረጃ ጀምሮ ያሉ መምህራን ለመጀመሪያ ደረጃ ለመጀመሪያው እርከን /ከ1-4/ ት/ቤት ርዕሰ መምህርነት ተወዳድረው በደረጃ ዕድገት ይመደባሉ።
- በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁና መስፈርቱን የሚያሟሉ ከመለስተኛ የመምህርነት ደረጃ ጀምሮ ያሉ መምህራን ለሙሉ የመጀመሪያ ደረጃ (ከ1-8) ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህርነት ተወዳድረው በደረጃ ዕድገት ይመደባሉ።
- በሁለተኛ ዲግሪ የማተርስ ዲግሪ የተመረቁና መስፈርቱን የሚያሟሉና ከመለሰተኛ የመምህርነት ደረጃ ጀምሮ ያሉ መምህራን ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና ለመሰናዶ ት/ቤቶች ርዕሰ መምህርነት ተወድድረው በደረጃ ዕድገት ይመደባሉ።
- በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቁና መስፈርቱን የሚያሟሉ ከመለሰተኛ መምህርነት ደረጃ ጀምሮ ያሉ መምህራን ርዕሣነ መምህራንና፣ ምክትል ርዕሣነ መምህራን ለመጀመሪያ ደረጃ (ከ1-8) ት/ቤት ሱፐርቫይዘርነት ተወድድረው በደረጃ ዕድገት ይመደባሉ።
- በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቁና መስፈርቱን የሚያሟሉ ከመለስተኛ መምህርነት ደረጃ ጀምሮ ያሉ መምህራን ርዕሣነ መምህራንና፣ ምክትል ርዕሣነ መምህራን ለአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና ለመሰናዶ ት/ቤቶች ሱፐርቫይዘርነት ተወድድረው በደረጃ ዕድገት ይመደባሉ።

ይህ መመሪያ ተሻሽሉ ተግባራዊ ከሆነበት ጊዜ ጀምሮ በአዲስ ተወዳድረው የሚመደቡ ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ለከፍተኛ ርዕሰ መምህርነትና ለከፍተኛ ሱፐርቫይዘርነት መወዳደር የሚችሉት የር/መምህርነትና የሱፐርቫይዘርነት ሥልጠና ሲያጠናቀቁ ብቻ ነው።በርዕሰ መምህርነት የደረጃ ዕድገት ተወዳድሮ በማገልገል ላይ ያለ የትምህርት ባለሙያ ለደረጃው የተፈቀደውን ደመወዝና ጥቅማ ጥቅሞች የሚያገኘው በሃላፊነት እስካለ ድረስ ብቻ ነው። በዚሁ መሠረት ባለሙያው በራሱ ጥያቄ ከሃላፊነቱ የሚለቅ ከሆነ ወይም በአቅም ማነስ ወይም በዲሲፒሊን ግድፈት ምክንያት ከሃላፊነቱ እንዲነሳ ሲደረግና ይህም በህጋዊ መንገድ የተረጋገጠ ሲሆን በሃላፊነቱ የሚያገኘው ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ይቋረጣል። ርዕሰ መምህሩ/ሯ ከተመደበበት/ችበት ሃላፊነት እንዲነሳ/ትነሳ ሲደረግ የስራ ምደባው በሲቪል ሰርቪስ መመሪያ መሰረት የሚፈጸም ሆኖ በዚሁ ውሳኔ መሰረት ርእሰ መምህሩ/ርቷ ወደ መምህርነት ሙያ የሚመለስ/ትመለስ ከሆነ ከምደባው ጎን ለጎን ተከታታይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ ስልጠና እንዲወስድ/ትወሰድ ይደረጋል።

S/N/N/P/R/G/Civil Service Agency

1.8. በየደረጃው የተዋቀረው የምልመላና ምደባ ኮሚቴ ኃላፊነትና ተግባር

1.8.1. ተወዳዳሪዎች የሚጋበዙበትን ማስታወቂያ ያወጣል። በሁሉም ት/ቤቶችና ተቋማት ማስታወቂያውን ያሰራጫል።

1.8.2. በማስታወቂያው ላይ፣

- የምዝገባ ጊዜ
- የምዝግባ ቦታ
- ተፈላጊ መስፈርቶች / የትም/ማስረጃ ፣ የአገልግሎት ዘመን
- ይዘው የሚቀርቧቸው ሌሎች ማስረጃዎች
- የጽሑፍ ወይንም የቃል ፈተና የሚሰጥበትን ቀንና ቦታ፣
- ሴት ተወዳዳሪዎች እንዲበረታቱ በትክክል የሚገልጽ ማሳሰቢያ አስፍሮ ያሰራጫሉ።

1.8.3. የጸሁፍም የሆነ የቃል ፈተና ያዘጋጃል የፈተናውን ሚስጥራዊነት እንዲጠብቅ ያደርጋል፣ የፈተና ወረቀቶቹን በጋራ ያሽጋል በጋራ ያርማል በውጤቱም ላይ ይፈራረማል።

1.8.4. ፈተናውን ለማረም ስታንዳርድ ያወጣል ማለትም ለጥያቄው የሚፈለጉ መልሶችንና ሊሰጥ የሚገባውን ነጥብ ለይቶ ያስቀምጣል።

1.8.5. የተወዳዳሪዎች ፕሮፋይል ያዘጋጃል/ ስለ እያንዳንዱ ተወዳዳሪ አጭር መግለጫ ያወጣል።

1.8.6. ውጤቱን ለሚመለከተው አካል ለማፅደቅ ያቀርባል።

S/N/N/P/R/G/Civil Service Agency

ለ/ *የሱፐርቫይዘሮች የእድገት መሰላል ስያሜዎች*

ተባባሪ ሱፐርቫይዘር፦ በሱፐርቫይዘር የደረጃ ዕድገት መሰላል ለመጀመሪያ ጊዜ ተወዳድሮበጀማሪነት ደረጃ የተመደበ የትምህርት አመራር ባለሙያ ነው።

ሱፐርቫይዘር፦ከተባባሪ ሱፐርቫይዘር ቀጥሎ በዕድገት የሚደረሰበት የትምህርት አመራር ባለሙያ ደረጃ ነው።

ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር፦ ከሱፐርቫይዘር ቀጥሎ በዕድገት የሚደረስበት የትምህርት አመራር ባለሙያ ደረጃ ነው።

መሪ ሱፐርቫይዘር፦ ከከፍተኛ ሱፐርቫይዘር ቀጥሎ በዕድገት የሚደረስበት የትምህርት አመራር ባለሙያ ደረጃ ነው።

ሐ/ *የምክትል ርእሰ መምህር የእድገት መሰላል ስሜዎች*

ጀማሪ ምክትል ርዕሰ መምህር፦ ስያሜው እንደሚያመለክተው በምክትል ርዕሰ መምህርነት ሙያ የመጀመሪያው ደረጃ ሲሆን ባለሙያው ለዚሁ ደረጃ ተወድድሮ በትምህርት አመራር ባለሙያነት የሚመደብበት የምክትል ርዕሰ መምህርነት መነሻ ደረጃ ነው። በት/ቤት አመራር በመጀመሪያ ደረጃ ተወዳድሮ/ሯ የተመደበ/ች የምክትል ርዕሰ መምህርነት መነሻ ደረጃ ነው።

ምክትል ርዕሰ መምህር፦ ከጀማሪ ምክትል ርዕሰ መምህርነት ቀጥሎ የሚደረስበት የት/አመራር ባለሙያ ደረጃ ነው።

ከፍተኛ ምክትል ርዕሰ መምህር/ት፦ ከምክትል ርዕሰ መምህርነት ቀጥሎ የሚደረስበት የትምህርት ቤት አመራር ባለሙያ ደረጃ ነው።

መሪ ምክትል ርዕሰ መምህር፦ ከከፍተኛ ምክትል ርዕስ መምህር ቀጥሎ የሚደረስበት የትምህርት ቤት አመራር ባለሙያ ደረጃ ነው።

2.2. ከአንዱ እርከን ወደሚቀጥለው እርከን ለመሸጋገር የሚያስፈልጉ የምደባ መስፈርቶች፣

በምክትል ርዕሰ መምህርነት፣ በርዕሰ መምህርነት እና በሱፐርቫይዘርነት መደብ ተወዳድረው ለመመደብ ከተመዘገቡት እጩዎች መካከል ተፈላጊውን ችሎታና መስፈርት የሚያሟሉትን ግልጽነት በሰፈነበት አሠራር በአግባቡ ለመምረጥ ይቻል ዘንድ የሚከተሉት የማወዳደሪያ መስፈርቶች ተዘጋጅተዋል።

ለርዕሰ መምህርነት የሚያበቁ መስፈርቶች፣

SNNPRG/Civil Service Agency

- ለደረጃው የሚያስፈልገውን የርዕሰ መምህርነት ስልጠና ያጠናቀቀ/ች
- በርዕሰ መምህርነት ተመድቦ/ባ በአገለገለባቸው/ችባቸው የመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት በአማካኝ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ያስመዘገበ/ች፣
- የርዕሰ መምህራን የደረጃ ዕድገት መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በርዕሰ መምህርነት ሁለት ዓመትና በላይ ሲያገለግሉ ቆይተው በ1996 ዓ.ም በጀማሪ ርዕሠ መምህርነት የተመደቡ ርዕሰ መምህራን ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ የርዕሰ መምህርነት የደረጃ ዕድገት ተይዞላቸው በቀጣይ ሦስት ዓመታት የአስመዘገቡት የአመራር ብቃታቸው ሲረጋገጥና በውጤት ተኮር ከፍተኛ የሥራ አፈጻጸም ውጤት ካስመዘገቡ በከፍተኛ የርዕሠ መምህርነት ደረጃ ይመደባሉ፣ ለደረጃው የተፈቀደውን የደመወዝ ክፍያም ያገኛሉ። እነዚህም ባለሙያዎች ለሙያው ሥልጠና ቅድሚያ ይሰጣቸዋል፣ ለሙያው የሚሰጠውን ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ አለባቸው።

3. ለመሪ ርዕሰ መምህርነት የሚያበቁ መስፈርቶች

- ከመምህራን ትምህርት ተቋም በርእሰ መምህርነት ሙያ ወይም በማስተማር ሙያ (Education) በማንኛውም የትምህርት ዓይነት በዲፕሎማ የተመረቀ/ች
- በከፍተኛ ርዕሰ መምህርነት 4 ዓመት ያገለገለ/ች
- በከፍተኛ ርዕሰ መምህርነት ተመድቦ/ባ በአገለገለባቸው/ችባቸው የመጨረሻዎቹ ሀለት ዓመታት በአማካኝ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ያስመዘገበ/ች፣
- የርዕሰ መምህርነት ሥልጠናን ያጠናቀቀ/ች፣

SNNPR/G/Civil Service Agency

- በርዕሰ መምህርነት ቢያንስ ሦስት ዓመት ያገለገለ/ች፣
- በርዕሰ መምህርነት ተመድቦ/ባ በአገለገለባቸው/ችባቸው የመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት በአማካይ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ያስመዘገበ/ች፣
- የርዕሰ መምህራን የደረጃ ዕድገት መመሪያ ከመውጣቱ በፊት በርዕሠ መምህርነት ሁለት ዓመትና በላይ ሲያገለግሉ ቆይተው በ1996 ዓ/ም *በጀማሪ ርዕሰ መምህራን* ከ1996 ዓ.ም ጀምሮ የርዕሰ መምህርነት የደረጃ ዕድገት ተይዞላቸው በቀጣይ ሦስት ዓመታት የአስመዘገቡት የአመራር ብቃት ሲረጋገጥና ከፍተኛ የሥራ አፈፃፀም ውጤት ከአስመዘገቡ *በከፍተኛ የርዕሰ መምህርነት* ደረጃ ይመደባሉ፣ ለደረጃው የተፈቀደውን የደመወዝ ክፍያ ያገኛሉ። እነዚህም ባለሙያዎች ለሙያው ሥልጠና ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። በሙያው ለመቀጠልም ለሙያው የሚሰጠውን ሥልጠና የመውሰድ ግዴታ አለባቸው።

መ. ለመሪ ርዕሰ መምህርነት የሚያበቁ መስፈርቶች

- ከመምህራን ትምህርት ተቋም በርእስ መምህርነት ሙያ ወይም በማስተማር ሙያ(Education) በማንኛውም የትምህርት ዓይነት በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ/ች፣
- በከፍተኛ ርዕሰ መምህርነት 4 ዓመት ያገለገለ/ች
- በከፍተኛ ርዕሰ መምህርነት ተመድቦ/ባ በአገለገለባቸው/ችባቸው የመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት በአማካኝ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ያስመዘገበ/ች፡
- የርዕሰ መምህርነት ሥልጠናን ያጠናቀቀ/ች፣

2.2.1.3 የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ የመሰናዶ ት/ቤቶች ርዕሰ መምህራን የምደባ መስፈርት፣

ሀ. ለጀማሪ ርዕሰ መምህርነት የሚያበቁ መስፈርቶች፣

- ከመምህራን ትምህርት ተቋም በርእሰ መምህርነት ሙያ ወይም በማስተማር ሙያ (Education) በማንኛውም የትምህርት ዓይነት በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቀ/ች
- ከተመረቀ /ች በኋላ በመምህርነት ሙያ ቢያንስ ሦስት ዓመት ያገለገ/ች በተጨማሪ ከማስተማር ሥራ ጎን ለጎን በዲፓርትመንት ተጠሪነት፣ በዩኒት

እነኚህም ባለሙያዎች ለሙያው ሥልጠና ቅድሚያ ይሰጣቸዋል። በመቀጠልም ለሙያው የሚሰጠውን ሥልጠና የመውሰድ ገዴታ አለባቸው ።

መ. ለመሪ ርዕሰ መምህርነት የሚያበቁ መስፈርቶች

- ከመምህራን ትምህርት ተቋም በርእስ መምህርነት ሙያ ወይም በማስተማር ሙያ (Education) በማንኛውም የትምህርት ዓይነት በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቀ/ች፣
- በከፍተኛ ርዕሰ መምህርነት 4 ዐመት ያገለገለ/ች
- በከፍተኛ ርዕሰ መምህርነት ተመድቦ/ባ በአገለገለባቸው/ችባቸው የመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት በአማካኝ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ውጤት ያስመዘገበ/ች፣
- የርዕሰ መምህርነት ሥልጠናን ያጠናቀቀች፣

2.2.1.3. **የመጀመሪያ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን /1-4- ምክትል ርዕሰ መምህራን የምደባ መስፈርት**

ሀ. ለጀማሪ ምክትል ርዕሰ መምህርነት የሚያበቁ መስፈርቶች፣

- ከመምህራን ትምህርት ተቋም በርእሰ መምህርነት ሙያ ወይም በማስተማር ሙያ (Education) በማንኛውም የትምህርት ዓይነት በዲፕሎማ የተመረቀ/ች፣
- ከተመረቀ/ች በኋላ በመምህርነት ሙያ ቢያንስ ሁለት ዓመት የሠራ/ች በተጨማሪም ከማስተማር ሥራ ጎን ለጎን በዲፖርትመንት ተጠሪነት፣ በተማሪዎች አመራርነት፣ በዩኒት አስተባባሪነት፣ በማዕከል ተጠሪነት ወይም በክበባት አስተባባሪነት ያገለገለ/ች፣
- በመምህርነት ባገለገለባቸው/ችባቸው በመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት በአማካይ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈፃፀም ያስመዘገበ/ች

ለ. ለምክትል ርዕሰ መምህር የሚያበቁ መስፈርቶች

ሀ/ ለጀማሪ ምክትል ርእሰ መምህርነት የሚያበቁ መሥፈርቶች

- ከመምህራን ትምህርት ተቋም በርእሰ መምህርነት ሙያ ወይም በማስተማር ሙያ (Education) በማንኛውም የትምህርት ዓይነት በመጀመሪያ ዲግሪ / የተመረቀ/ች /
- ከተመረቀ/ች/ በኋላ በመምህርነት ሙያ ቢንስ ሁለት ዓመት የሠራ/ች/ በተጨማሪም በዩኒት መሪነት ፣ በዲፓርትመንት ተጠሪ፣ በተማሪዎች አመራርነት፣ በማዕከል ተጠሪነት ወይም በክበባት አስተባባሪነት የሠራ/ች/
- በመምህርነት ባገለገለባቸው /ችባቸው / በመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት በአማካይነት ከፍተኛ ውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ያስመዘገበ/ች/

ለ/ ለምክትል ርእሰ መምህርነት የሚያበቁ መሥፈርቶች

- ከመምህራን ትምህርት ተቋም በርእሰ መምህርነት ሙያ ወይም በማስተማር ሙ ያ /Education / በማንኛውም የትምህርት ዓይነት በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ/ች/
- በጀማሪ ምክትል ርእሰ መምህርነት ቢያንስ 2 ዓመት ያገለገለ/ች/
- ለደረጃ የሚያስፈልገውን የምክትል ርእሰ መምህርነት ሥልጠና የወሰደ/ች/ ወይም ለውድድር የሚያበቃውን/ትን አግባብነት ያለው የሙያ ብቃት መግለጫ የቅርብ ኃላፊ ከሆነው አካል በጽሁፍ ማቅረብ የሚችል/ የምትችል/
- በጀማሪ ምክትል ርእሰ መምህርነት ባገለገለባቸው/ችባቸው የመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት በአማካይ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ያስመዘገበ/ች/

- ከተመረቀች በኋላ በመምህርነት ሙያ ቢያንስ ሁለት አመት የሠራ/ች/ በተጨማሪም በዩኑት መሪነት፣ በዲፓርትመንት ተጠሪነት በክበባት አሰተባባሪነት በተማሪዎች አመራርነት ያገለገለ/ች/
- በመምህርነት ባገለገለባቸው / ችባቸው / በመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት በአማካይ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ያስመዘገበ

ለ/ ለምክትል ርእሰ መምህር የሚበቁ መሥፈርቶች

- ከመምህራን ትምህርት ተቋም በርእሰ መምህርነት ሙያ ወይም በማስተማር ሙያ (Education / በማንኛውም የትምህርት ዓይነት በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቀ/ች /
- በጀማሪ ምክትል ርእሰ መምህርነት ቢንስ 2 ዓመት ያገለገለ/ች
- ለደረጃ የሚያሰፈልገውን የምክትል ርእሰ መምህርነት ሥልጠና ያጠናቀቀ/ች
- በጀማሪ ምክትል ርእሰ መምህርነት ባገለገለባቸው/ችባቸው በመጨረሻዎቹ ሁለት አመታት በአማካይ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸመም ያስመዘገበ/ች /

ሐ/ ለከፍተኛ ምክትል ርእሰ መምህርነት የሚያበቁ መሥፈርቶች

- ከመምህራን ትምህርት ወይም ተቋም በርእሰ መምህርነት ሙያ ወይም በማስተማር ሙያ / Education / በማንኛውም የትምህርት ዓይነት በመጀመሪያ ወይም በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቀ /ች /
- በምክትል ርዕሰ መምህርነት ቢያንስ 4 ዓመት ያገለገለ/ች
- በከፍተኛ ምክትል ርእሰ መምህርነት ባገለገለው /ችባቸው በመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት በአማካይ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ያስመዘገበ/ች/
- ለደረጃው የሚያስፈልገውን የምክትል ርዕሰ መምህርነት ሥልጠና ያጠናቀቀ/ች

- በተባባሪ ሱፐርቫይዘትርነት በአገለገለባቸው/ችባቸው የመጨረሻዎች ሁለት ዓመታት በአማካይ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ያስመዘገበ/ች /
- ለደረጃ የሚያስልገውን የሱፐርቫይዘርነት ሥልጠና የወሰደ/ች

ሐ/ ለከፍተኛ ሱፐርቫይዘርነት የሚያበቁ መሥፈርቶች

- ከመምህራን ትምህርት ተቋም በሱፐርቫይዘርነት ሙያ ወይም በማስተማር ሙያ /Education /በማንኛው የትምህርት ዓይነት በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ/ች
- በሱፐርቫይነት ደረጃ በተከታታይ ለሦስት አመታት ያገለገለ/ች /
- በሱፐርቫይዘርነት በአገለገለባቸው /ችባቸው የመጨረሻዎች ሁለት ዓመታት በአማካይ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ያስመዘገበ/ች /
- ለደረጃ የሚያስፈልገውን የሱፐርቫይዘርነት ሥልጠና ያጠናቀቀ/ች /

መ/ ለመሪ ሱፐርቫይዘርነት የሚያበቁ መሥፈርቶች

- ከመምህራን ትምህርት ተቋም በሱፐርቫይዘርነት ሙያ ወይም በማስተማር ሙያ /Education / በማንኛውም የትምህርት ዓይነት በመጀመሪያ ዲግሪ የተመረቀ/ች
- በከፍተኛ ሱፐርቫይዘርነት በተከታታይ አራት አመታት ገለገለ/ች /
- ለደረጃ የሚያስፈልገውን የሱፐርቫይዘርነት ሥልጠና ያጠናቀቀ/ች
- በከፍተኛ ሱፐርቫይዘርነት በሠራባቸው/ችባቸው በመጨረሻዎች ሁለት አመታት በአማካይ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ

SNNPR/G/Civil Service Agency

ሐ/ ለከፍተኛ ሱፐርቫይዘርነት የሚያበቁ መሥፈርቶች ፣

- ከመምህራን ትምህርት ተቋም በሱፐርቫይከርነት ሙያ ወይም በማስተማር ሙያ /Education / በማንኛውም የትምህርት ዓይነት በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቀ /ች /
- በሱፐርቫይዘርነት ደረጃ ለሶሰት ተከታታይ አመታት የሠራ/ች /
- በሱፐርቫይዘነት ባገለገለባቸው/ችባቸው በመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት ውሰጥ በአማካይ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም ያስመዘገበ/ች
- ለደረጃው የሚሰጠውን የሱፐርቫይዘርነት የሙያ ሥልጠና ያጠናቀቀ/ች

መ/ ለመሪ ሱፐርቫይዘርነት የሚያበቁ

- ከመምህራን ትምህርት ተቋም በሱፐርቫይዘርነት ሙያ ወይም በማሰተማር ሙያ /Education / በማንኛውም የትምህርት ዓይነት በሁለተኛ ዲግሪ የተመረቀ/ች
- በከፍተኛ ሱፐርቫይዘርነት በተከታታይ አራት አመታት ገለገለ/ች /
- ለደረጃው የሚያስፈልገውን የሱፐርቫይርነት ሥልጠና ያጠናቀቀ/ች
- በከፍተኛ ሱፐርቫይዘርነት በሠራባቸው /ችባቸው በመጨረሻዎቹ ሁለት አመታት በአማካይ ከፍተኛ የውጤት ተኮር የሥራ አፈጻጸም

SNNPRG Civil Service Agency

3.2 የመጀመሪያ ደረጃ፣ የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ ት/ቤቶች ምክትል ርዕሰ መምህራን ደመወዝ ስኬል

ተ.ቁ	ደረጃ	የደረጃ ከፍታ	መነሻ ደመወዝ
1	የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል/ 1-4/ ት/ቤት ምክትል ርዕሰ መምህር የደመወዝ ስኬል		
	ጀማሪ ምክትል ርዕሰ መምህር	I	1228.00
	ምክትል ርዕሰ መምህር	II	1410.00
	ከፍተኛ ምክትል ርዕሰ መምህር	III	1617.00
	መሪ ምክትል ርዕሰ መምህር	IV	1851.00
2	የመጀመሪያ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል እና ሙሉ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት / 5-8/ /1-8/ ምክትል ርዕሰ መምህር የደመወወዝ ስኬል		
	ጀማሪ ምክትል ርዕሰ መምህር	III	1410.00
	ምክትል ርዕሰ መምህር	IV	1617.00
	ከፍተኛ ምክትል ርዕሰ መምህር	V	1851.00
	መሪ ምክትል ርዕሰ መምህር	VI	2115.00
3	የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና የመሰናዶ/ 9-10፣ 11-12/ ምክትል ርዕሰ መምህር የደመወዝ ስኬል		
	ጀማሪ ምክትል ርዕሰ መምህር	V	1851.00
	ምክትል ርዕሰ መምህር	VI	2115.00
	ከፍተኛ ምክትል ርዕሰ መምህር	VII	2417.00
	መሪ ምክትል ርዕሰ መምህር	VIII	2762.00

3.3 የመጀመሪያና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሱፐርቫይዘሮች የደመወዝ እስኬል

ተ.ቁ	ደረጃ	የደረጃ ከፍታ	መነሻ ደመወዝ
1	የመጀመሪያ ደረጃ ሱፐርቫይዘር		
	ተባባሪ ሱፐርቫይዘር	IV	1617.00
	ሱፐርቫይዘር	V	1851.00
	ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር	VI	2115.00
	መሪ ሱፐርቫየዘር	VII	2417.00
2	የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሱፐርቫይዘር		
	ተባባሪ ሱፐርቫይዘር	VI	2417.00
	ሱፐርቫይዘር	VII	2762.00
	ከፍተኛ ሱፐርቫይዘር	VIII	3152.00
	መሪ ሱፐርቫይዘር	IX	3597.00

ማሳሰቢያ፦ አንፃራዊ መስናዶ የጕደላቸውና ቆላማ አካባቢዎች ተብለው በክልሉ መንግሥት ተለይተው ባሉ ወረዳዎች የሚመለመሉ ር/መምህራን፣ ም/ር/መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በደንብ ቁጥር 35/97 አንቀፅ 8 እና 9 ላይ የተመለከተው ጥቅማቸው ይከበርላቸዋል።

ደ/ብ/ብ/ህ/ክ/መንግሥት ሲቪል ሰርቪስ ኤጀንሲ SNNPRG ... Agency

ምዕራፍ አራት

የርዕሰ መምህራንና የሱፐርቫይዘሮች የሥራ ዝርዝር

4.1 ርዕሰ መምህር

- የትምህርት ቤት መሻሻል እቅዶችን ማውጣትና አተገባበሩንም መከታተል፣
- የትምህርት ቤቱን አመታዊ እቅድ ከወረዳውና ከክልሉ ዕቅድ በመነሳት ማዘጋጀትና መተግበር፣
- የትምህርት ቤቱን አካዳሚክና አስተዳደራዊ ስራ መምራት፣
- ትምህርት ቤቱን በመወከል ማንኛውንም ስምምነት መፈፀም፣
- የትምህርት ቤቱን ንብረት የሰው ሀይልና ፋይናንስ በአግባቡ ሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ ፣
- የመምህራን ልማት መርሀግብርን በተሟላ መልኩ መምራት፣
- በት/ቤት ደረጃ የሚተገበሩ የመምህራን ልማት መርሀ ግብር ዝርዝር ፕሮግራሞችን ማቀድ፣ መፈፀምና የክትትል ስርዓት መዘርጋት ፣
- በት/ቤት ደረጃ የሚሰጡ የተከታታይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም የስልጠና ፍላጐቶችን በመለየት ኮርሶች እንዲዘጋጁና ጥራቱን የጠበቀ ስልጠና እንዲሰጥ ማመቻቸት፣
- ለተከታታይ ሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም ተግባራዊነት ቁልፍ ሚና የሚኖራቸውን ኮሚቴዎች ማደራጀት፣
- በየዓመቱ የሚሰጡ የመምህራን ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችን በትምህርት ቤቱ መደበኛ ዕቅድ ውስጥ በቁልፍ ተግባርነት ተካተው መከናወናቸውን መከታተል ማረጋገጥ፣
- ለተከታታይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም ስኬታማነት በሙሉ ኃላፊነት መንቀሳቀስ፣
- በአመቱ በት/ቤቱ የተከናወኑ ተግባራትን በሚመለከተው የተጠናከረ መረጃ ማደራጀት፣ መያዝና ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማድረግ ፣
- የተከታታይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበርን ከት/ቤቱ ማህበረሰብ ጋር መገምገም፣

- በየአመቱ የሚሰጡ የመምህራን ተከታታይ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎችን በትምህርት ቤቱ መደበኛ ዕቅድ ውስጥ በቁልፍ ተግባርነት ተካተው መከናወናቸውን መከታተል፣
- በዓመቱ በት/ቤቱ የተከናወኑ ተግባራትን በሚመለከተው የተጠናከረ መረጃ ማደራጀት መያዝና ማጠናቀር፣
- ከርዕሰ መምህሩ ጋር በመሆን የተከታታይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበርን ከት/ቤቱ ማህበረሰብ ጋር መገምገም፣
- የት/ቤቱ መምህራንን የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ ክትትል ማድረግና ተገቢውን ድጋፍ መስጠት ፣
- በት/ቤቱ ውጤት ተኮር ዕቅድ ዝግጅት ለርዕሰ መምህሩ ተገቢውን መረጃ ማቅረብና በዕቅድ ዝግጅቱ ሙሉ ተሳትፎ ማድረግ፣
- በት/ቤት ደረጃ መቋቋም የሚገባቸውን የተለያዩ የትምህርት ክፍሎችን ፣ ኮሚቴዎችንና ተጓዳኝ ክበባትን ማደራጀትና የሥራን እንቅስቃሴአቸውን በመከታተል ድጋፍ መስጠት ፣

- ከላይ የተቀመጡት የሥራ መዘርዝሮች በሁሉም ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ምክትል ርዕሰ መምህራን የሚያገለግሉ ናቸው ። ሆኖም ከየደረጃው የሚጠበቀው የአፈፃፀም ብቃት በሚዘጋጀው የአመራሮች ብቃት ስታንዳርድ ይገለፃል።

4.3 ሱፐርቫይዘር

- የት/ቤቶች የት/ቤት መሻሻል የሶስት ዓመት ጥቅል ዕቅድና የአንድ ዓመት ዝርዝር ፕሮግራም ማውጣታቸውንና አዘገጃጀቱም በስታንዳርዱ መሠረት መሆኑን መከታተልና ድጋፍ መስጠት ፣
- ት/ቤቶችና የጉድኝት ማዕከላት በአወጡት ዝርዝር መሠረት እየሰሩ መሆኑን መከታተልና ድጋፍ መስጠት ፣
- የት/ቤቶች ዝርዝር አመታዊ ዕቅድና ከክልልና ከወረዳው ዕቅድ በመነሳት መዘጋጀቱን መከታተል፣ መረጃ መያዝና ሪፖርት ማድረግ ፣
- የት/ቤት መሻሻልና የመምህራን ልማት መርሀ ግብርን ማስተዋወቅ፣ መደገፍ፣ መከታተል፣

ምዕራፍ አምስት

በርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሥራና የደረጃ ዕድገት አፈፃፀም ከባለድርሻዎች የሚጠበቅ ኃላፊነትና ተግባር

5.1 ትምህርት ሚኒስቴር

- የርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ምልመላና ምደባ መመሪያ ያዘጋጃል፣
- የርዕስ መምምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሥልጠና ስታንዳርድ ይዘጋጃል፣
- የርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሥራ ብቃት ስታንዳርድ ያዘጋጃል ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ የጥራት ደረጃውን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አዳዲስ ስታንዳርዶችን አሻሽሎ ያዘጋጃል፣
- የተሰበሰቡ የክትትል መረጃዎችን መሠረት በማድረግ በዓመት አንድ ጊዜ ከክልል ትም/ቢሮዎች ጋር ምክክር በማድረግ ውሳኔ ያሰጣል፣
- የርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን ፕሮፋይል ያወጣል፣ ይወሳናል፣

- **የክልል ትምህርት ቢሮ**

- በፌደራል ደረጃ የተዘጋጀውን የርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ምልመላና ምደባ መመሪያ መሠረት በማድርግ ክልል ተኮር የሆነ መመሪ ያዘጋጃል፣
- በፌደራል በወጣው የሥልጠና ስታንዳርድ መሠረት በክልል የሚካሄደውን ሥልጠና ይከታተላል፣
- ሥልጠናውን ላጠናቀቁና መስፈርቱን ለሚያሟሉ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ለደረጃው የተመደበውን ደመወዝና ማትጊያ እንዲያገኙ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል ይቆጣጠራል፣
- በተዘጋጀው የብቃት ስታንዳርድ መሠረት ርዕሰ መመምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ኃላፊነታቸውን በብቃት መወጣታቸውን ይቆጣጠራል፣
- በክልል ትምህርት ቢሮ ደረጃው የሚመደበው ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮችን ካለ ይመድባል ።

SNNP/R/G/Civil Service Agency

- ለርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ደመወዝና ማትጊያ በጀት በመያዝ መስፈርቱን አሟልተው ለተመደቡት ክፍያ ይፈጽማል፣
- ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች በሚጠበቅባቸው ፕሮፋይል አኳያ ተግባራቸውን በብቃት ማከናወናቸውን ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ መረጃዎችንም በመያዝ ለሚመለከተው ክፍል ሪፖርት ያደርጋል፣
- ሙያውን በሚመለከት አዳዲስ አሰራሮችን ማስፈን አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በስልጠናው ውስጥ እንዲካተት አስተያየት ያቀርባል፣
- በየት/ቤቶች የተገኙ የአመራርና የድጋፍ አሰጣጥ መልካም ተሞክሮዎችን ልምድ ያለዋውጣል አስፋፍቶ ይጠቀማል።

ምዕራፍ ሰባት

መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ የትምህርት ቤት አመራር አካላትን ምርጫ ምደባና ደመወዝ በተመለከተ የተዘጋጀ ሲሆን መመሪያው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በክልሉ ትም/ቢሮ የሚሻሻል ይሆናል።

ምዕራፍ ስምንት

የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የትምህርት ቤት አመራር ተብለው የሚጠሩ ርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች ባሉባቸው የሴክተሩ ትምህርት ቤቶችና መሥሪያ ቤቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

ምዕራፍ ዘጠኝ

የተፈፃሚነት ጊዜ

ይህ የርዕሰ መምህራንና ሱፐርቫይዘሮች የሥራ ዕድገትና የደመወዝ ምደባ መመሪያ ከሐምሌ 1/2000 ጀምሮ የፀና ይሆናል።

S/N/N/P/R/G/Civil Service Agency